# ፍትህ በራቃት ምድር ፍትህ የጎደለው ትግል:- የኢትዮጵያ ፖለቲካ እስረኞች ጉዳይ

ደ. በፈቃዱ

ይህችን አጭር ጽሁፍ እንዳቀርብ ያገፋፋኝ ምክንያት በ1997 ዓ/ም ብሔራዊ ምርጫ ወያኔ ከተሸነፈ ወዲህ ያሰራቸውን እስረኞች ለማስፈታት በሚደረገው ትግል ዙሪያው የሚታየው አድሎ የተሞላበትና ፍትሕ የጎደለው እንቅስቃሴ ነው። የእንቅስቃሴው መሪህ ሃሳብ የሚለው "መሪዎቻችን ይፈቱ!" ሲሆን ትግሉም "መሪዎቻችንን እናስፈታ!" "መሪዎቻችንን ለማስፈታት..." ወዘተ ነው። ታዲያ እዚህ ጋ የት ላይ ነው አድሎና ፍትሕ የጐደለው? የሚሉና ሌሎችም ጥያቄዎች በብዙዎቻችሁ ጭንቅላት እንደምመላለሱ ይገባኛል። አንዳንዶቻችህ በጥያቄዎች ብቻ ሳትወሰኑ ገና ጽሁፌን ሳታነቧት ከመደምደሚያው ላይ በመድረስ የተለያዩ ስሞችን (ወያኔ ፤ ከሃዲ ፤ ቅጥረኛ... ወዘተ) ልትለጥፉብኝ እንደምትችሉም ይገባኛል።

ሕልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርምና ፤ ምንም ጭብጥ የማይኖረውን ክስ ፈርቶ እውነትን ሳይናገሩ ማለፍ የህሊና ፀፀት ከመሆኑም ባሻገር ይህ የተዛባ አካሄድ ወያኔን ለመጣል በሚደረገው ትግል ላይ እያሳደረ ያለው አሉታዊ ተፅዕኖ እንዲቀጥል ያደረጋል። ስለዚህ የጽሁፌ ዋና ዓላማ ትግሉ ተስተካክሎ ወሳኝ የሆነ ውጤት ማስገኘት በሚችልበት መልኩ እንዲቀናጅ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በሙሉ ፤ የሙያ ማህበራት ፤ ሰብአዊና ማህበራዊ ድርጅቶች በጋራ እንዲሰሩ ለመገፋፋት ነው እንጂ እላይ በተጠቀሰው መልክ የምንቀሳቀሱትን ወገኖች ለመተቸት ብቻ የታሰበ እንዳልሆነ አንባቢያን እንድረዱልኝ አሳስባለሁ።

## የወያኔ አስተዳደርና የፖለቲካ እስረኞች

ወያኔ ፤ በደርግ ፕሮፓጋንዳና ምክንያት ያኮረፉ ምዕራባዊያን አገሮችና የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች በሰጡት ድጋፍ በ1991 ዓ/ም የሃገሪቱን በትረ-ስልጣን ከጨበጠበት ጊዜ አንስቶ የግፍ ጭፈጨፋዎችን ፤ የጐሣ ምንጠራና የዘር ማጥፋት ዘመቻ አካሂዷል። የአገር ክህደት ወንጀልም ፈጽሟል።

እየፈጸመም ነው። ይህም አዲስ አበባ ሲገባ ወይም ከገባ ወዲህ ብቻ ያሳየው ጨካኝ ባሕሪይው ሳይሆን ገና ወያኔ በወያኔነት መንቀሳቀስ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ አብረው ያደገና የኖረ ጭካኝነትና ፀረ-ኢትዮጵያዊነት ባህሪው ነው። ወያኔ ባጠቃላይ የኢትዮጵያን ህዝብ በሽብር የሚያስተዳድር ጐሜኛ-ፋሽስት መንግሥት እንደሆነ እንኳን የጭቆናና የግፍ ቀንበር ተሸክሞ ያለው የኢትዮጵያ ህዝብ ቀርቶ ራሱ ወያኔም ሆነ ደጋፊዎቹ መንግሥታት ጠንቅቀው የሚያውቁት ሓቅ ነው። ይሁን እንጂ ግፉ ይቁም ፤ ግድያው ያብቃ ፤ ሰብአዊ መብት ይከበር ፣ ዴሞክራሲያዊ መንግስት ይቋቋም ወዘተ የሚሉትንና ሌሎችንም ህጋዊ ጥያቄዎችን ያነሱት ኢትዮጵያውያኖችን በተገላብጦሽ በፀረ-ሰላም ፣ በሽብርተኛነት ፣ በዘር ማጥፋትና በሃገር ክህዴት ወንጀል በመክሰስ በሽህ የሚቆጠሩ ዜጎችን አሥሯል። ግማሾቹን የረዥም ጊዜ የእስራት ፍርድ በይኖባቸው ጊዜያቸውን ሳይጨርሱ ሙተው ሬሳቸውን አውጥተው ይጥላል ወይም ልሞቱ ሲሉ ፈታሁ ለማለት ያህል በድን የሆነ ገላ አውጥተው ለቤተሰብ ያስረክባሉ። ለምሳሌ የመላው አማራ ድርጅት መሥራችና ፕረዝዳንት የነበሩት ፕሮፈሰር አስራት ወልደየስ። እግዚአብሔር ጤናና ዕድሜ ሰጥቷቸው የተፈረደባቸውን ጊዜ ጨርሰው የወጡትም ከጥቅት ቀናት ወይም ሳምንታት በሁዋላ በሌላ የፈጠራ ወንጀል ተይዘው እንደገና የረዥም ጊዜ እሥራት የተፈረደባቸውም አሉ። ለምሳሌ አቶ አበራ የማነአብን መጥቀሱ ይበቃል።

ሌሎቹ ደግሞ ፍርድ ቤት የመቅረብ እድል ሳያገኙ እንዲሁ ተረስተው የቀሩም አሉ። ከነአካተው በሕይወት መኖራቸውም ሆነ የታሠሩበት እሥር ቤት ሳይታወቅ በወያኔ እጅ የሚማቀቁም ቁጥራቸው ከፍተኛ ነው። በተለይም የኢህአፓ አመራሮችና የፓርት አባላት ቁጥራቸው ከፍተኛ እንደሆነ ይታወቃል። ጥቅቶቹን ለመጥቀስ ያህል ፀጋዬ ገ/መድህን (ደብተራው) ፤ ይስሐቅ ደብረፅዩን ፤ ስጠታው ሁሴን ፤ አምሃ በለጠ፤ አዛናው ደምሌ ፤ ተክላይ ገ/ስላሴ ፤ አበራሽ በርታ ፤ ታደለ መንገሻና ሌሎችም በመቶ የሚቆጠሩ በወያኔ ወህኒ ቤት አሉ። በብዙ የሚቆጠሩ ኦሮሞ ብሔረሰብ ተወላጆችና ሌሎችም የመብት ታጋዮች ያለፍርድ ታስረዋል። በዚህ መልክ በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ የህሊና እስረኞች በተለያዩ የሃገሪቱ ወህኒ ቤቶች አሉ። ስለእነዚህ የረጅም ጊዜ የፖለቲካ እስረኞች በሰብአዊ መብት ተካራካሪነት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀሰው ኢሰመጉ እንኳን አላየሁም አልሰማሁም ማለትን እንደመረጠ ጠቁመው ማለፉ አስፈላጊ ነው። በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ የፓለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ

ለሁሉም እስረኞች ድምፅና ተከራካሪ ጠበቃ ሆኖ ያደረገውና እያደረገ ያለው አስተዋፅኦ የሚደነቅ መሆኑን ጠቁሜ ማለፍ እፈልጋለሁ።

ከምርጫ 1997 ወዲህ በብዙ ሺህ የሚቆጠረው ህዝብ በጅምላ መታሰሩ ግልጽ ነው። ከእነዚህ ውስጥ በያዙት ድርጅታዊ ሃላፊነትና በሙያቸው ዝና ያተረፉ ጥቂቶቹ ብቻ ናቸው። በዚህ ገባ ሳይባል ሀገሩንና ወገኑን ለመታደግ ብሎ አነስተኛ ደመወዝ እየተከፈለው ቤተሰቡን ከሚያስተዳድርበት ሥራ ገበታው ወጥተው በትግሉ በመሳተፍ ወይም ለተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ድጋፍ በመስጠቱ ብቻ ከሥራው ተፈናቅለው እሥር ቤት ተወርውረው ቤተሰቦቻቸው ሜዳ ላይ የወደቁባቸው ፤ ግን የማንንም ጠበቃነት ወይም ተካራካሪነትን ያልታደሉና ተረስተው የቀሩ ቁጥራቸው በሽህ የሚቆጠር ነው። ታዲያ ለእነዚህ ማን ይከራከርላቸው? እነዚህን ሁሉ ረስተው ለጥቂት ዝነኞች ብቻ መፈታት መከራከርና ለእነሱ ብቻ ስንቅ ካላቀበልን ብለው መሯሯጥ ተስተውሏል። ይህ ደግሞ የቡድን ስሜት ከማጠናከርና የአንድነትን ስሜት ከማኮላሸት በስተቀር ለእስረኞች መፈታትም ሆነ ለአንድነት ያበረከተው ወይም የሚያበረክተው አስተዋጽኦ አለ ብዬ አላምንም። ወያኔ በውዴታ እስረኞችን ስለማይፈታና ሥልጣኑንም ስለማይለቅ በአንድነት ትግሉን ከማፋፋም በስተቀር ሌላ አማራጭ የለንም ብዬ አምናለሁ። ይህ ወሳኝ የሆነውን የትግል ስልት አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶች በቃል እንደዳዊት እየደጋገሙ ግን በተግባር ተቃራኒውን ከመፈጸም አልፎ እርስበርስ ሲወነጃጀሉ ማየትና መስማት ወገነን የሚያሳዝን ግን ወያኔን የሚያስደስት አሳዛኝና አሳፋሪ ተግባር ነው። ይህ ደግሞ ለታሰሩትም ሆነ ለአንድነት ትግል የሚሰጠው ፈይዳ እንደሌለው ልታወቅ ይገባል።

## <u>እስረኞችን ለማስፈታትና ለመርዳት የሚደረገው ትግል</u>

እስረኞችን ለማስፈታት የሚደረገው ትግል የወያኔን ፍላጎት እያረካ ያለ ይመስለኛል። በተጨማሪም የተያየዘው የትግል ስልት ላለው ጨምር ዓይነት ሆነና የታዋቂዎችን ስም ብቻ የሚጠራ ሆኖ ስንብቷል። በሌላ መልኩ ደግሞ ምንም ታዋቂ ቢሆኑም ወይም እጅግ ከፍ ያለ መስዋዕነት ቢከፍሉም የራስ ፓርቲ አባል ያልሆነ ሁሉ የተረሳበት ሁኔታ ይታያል። በተለያዩ ድረ-ገፆች የሚናያቸው ጥሪዎች Free Nega, Free Mesfin, Free Yacob, …ወዘተ ሲሆን ይህ አካሄድ በአንድነት ትግል ዙሪያ ልሰጥ የሚችለው ጥቅም እነዚህ ግለሰቦች

አባል ከሆኑበት ድርጅት ያለፈ አይሆንም የሚል ስጋት አለኝ። ይሁንና አንድ ግልፅ እንድሆንልኝ የሚፈልገው ነገር ቢኖር ፀረ-ወያኔ የሆነ ግለሰብም ሆነ ድረጅት የቅንጅት መሪዎችን መፈታት የማይፈልግ የለም ብዬ አምናለሁ። እኔ አስምረበት ማለፍ የምፈልገው ነገር ቢኖር የተያያዘው የትግል ስልት ልያስፈታቸው የሚችል አለመሆኑን ነው። ሌላው መጠቀም ይህ አካሄድ የሳተው ትልቁ ቁም ነገር ቢኖር የኢትዮጵያ ህዝብ በሙሉ እስረኛ መሆኑን ነው። በተጨማሪም ወያኔ እስረኞችን በውዴታ የማይፈታቸው መሆኑን ከግምት ውስጥ ያላስገባ ስልት ነው ብዬ አምናለሁ። በመጨረሻም "መሪዎቻችን ፈታልን" ወያኔ መስማት የሚፈልገው መዝሙር ነው። ትግሉ ከ"ሥልጣን አስረክብ!" ፤ "የህዝብ ድምፅ ይከበር!" ወደ እስረኞችን ፈታልን ዝቅ ማለቱ ለወያኔ አንድ ትልቅ እፎይታ ነው።

በተለያዩ ክፍለ ዓለማት በቅንጅት ስም የሚንቀሳቀሱ ቡድኖች ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ አንዳንድ ግለሰቦች ቀደም ሲል ከደርግና ከኢህአፓ እንዲሁም ከሌሎችም ድርጅቶች ውስጥ የነበረውን ቅራኔ በማራገብ በእንቅስቃሴው የቅንጅት ስም ብቻ መጠራት አለበት ብለው የታገሉበትና የሚታገሉበት ሁኔታም ይስተዋላል። ለምሳሌ ስለእስረኞች ሲናገሩ ከቅንጅት መሪዎች በስተቀር ሌላ እንዳልታሰረ አድርገው ለማቅረብም ይሞክራሉ። በስንት ግፊት ሁሉም እስረኞች ይፈቱ የሚለውን በመፍክራቸው ውስጥ ለማካታት በገደዱም ሁሉም እስረኞች ይሉና "የቅንጅት መሪዎች" ፤ "ጋዜጠኞች" እና "የሲቪክ ማህበራት መሪዎች/አባለት" ብለው ቆጠራውን ያቆማሉ። ለሎቹስ የት ቀሩ? ከምርጫ 97 በፊት የታሰሩት እስረኞች መውጣት የለባቸውም? ከምርጫ 97 ወዲህ የታሰሩና እላይ በተጠቀሱት ቡድኖች ውስጥ የማይካታቱስ ለማን ይቀራሉ? ለነገሩ በኢትዮጵያ ውስጥ ፓለቲካንና የፓለቲካ ትግልን ያመጣው ወያኔ ነው ብለው ምንም ለአፋቸው ሳይከብዳቸው የተናገሩና እጃቸውን ሳይሰለቻቸው የጻፉ ምሁራን ብቅ ባሉበት ዘመን ፤ ከፋሽቶችና ከባንዳዎች ስፋለሙ ተይዘው የታሰሩትን አላየንም ወይም አልሰማንም ብሉ ወይም ስለእነሱ መናገር ቢከብዳቸው የሚደንቅ ነገር አይሆንም። ስለእነዚያ ብርቅ ልጆች አንደበታቸው አልናገር ያለው እጃቸውም ብዕር አንስቶ መጻፍ የከበደው ያላንዳች ምክንያት እንዳልሆነ ነው የሚረዳኝ።

## የ"መሪዎቻችን ይፈቱ" ድክመት

ይህ በተወሰኑት ግለሰቦች ያነጣጠረውና የአንድ ፖለቲካ ድርጅት አባላት የሆኑትን እስረኞች ለማስፈታት የሚደረገው ትግል በአንድነት መንፈስ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አለው ብዬ አምናለሁ። ከየሥራ ገበታው ተፈናቅለው ለታሰሩት ሰዎች ምንም ነገር አለመደረጉን ቤተሰቦቻቸው ፤ ጓደኞቻቸውና የሚያውቋቸው ሁሉ ሲረዱ ለወደፊት በትግሉ የመሳተፍ ፍላጎታቸው ዝቅ ይላል። በሌላ በኩል ደግሞ ለወያኔ ፕሮፓጋንዳ የመጋለጥ አደጋም ከፍተኛ ነው።

በተጨማሪም ይህ አካሄድ በወያኔ ጫና እንዲያደረጉ ያተኮረባቸው አገሮች በተለይም አሜሪካና እንግሊዝ ወያኔን በሥልጣን ያስቀመጡ አገሮች ከመሆናቸው በላይ የኢትዮጵያን መጠናከርና መልማት እንዲሁም ሰላም ማግኘት የማይፈልጉ መሆናቸውን በርካታ የታሪክ መስፍርቶች ያመለክታሉ። ወያኔ ምንም ወንጀል ያልፈጸሙ የሙብት ታጋዮችን ፤ የፓለቲካ ድርጅት መሪዎችን ፤ ጋዜጠኞችንና የተቃዋሚ የፓለቲካ ድርጅቶች አባላትንና ደጋፊዎችን በተገላብጦሽ በመሰረተባቸው ፈጠራ ወንጀል ከሰሰው ብዙዎቹን ለረጅም ጊዜ ያለፍርድ በእስር ቤት ሲያሰቃያቸውና የተወሰኑትን ረጅም ጊዜ እስራት ሲፈርድባቸው አሜሪካና እንግሊዝ እኛ አላየንም አልሰማንም ማለትን ነበር የመረጡት።

ሌላው ቢቀር ከምርጫ 97 ጋር በተያያዘ "ወንጀል" ለታሰሩት አሜሪካና እንግሊዝ እውነት ለዴሞክራሲና ለሰብአዊ መብት የቆሙ ቢሆኑ ኖሮ ያለምንም ቅደሚ ሁኔታ ከሌሎች የፖለቲካ እስረኞች ጭምር እንዲፈታቸው በወያኔ ላይ ጫና ማደረግ ሲገባቸው አለማደረጋቸው የሚያመለክተው ለወያኔ የሚሰጡትን ገደብ-የለሽ ድጋፌ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ባሁኑ ሰዓት ፍትሕ አለመኖሩን እያወቁ የአሜሪካና የእንግሊዝ መንግሥታት ለመለስ የሰጡት ትዕዛዝ "ፌትሃዊ ፍርድ ስጣቸው" ነው። የቀድሞ ወዳጃቸውን ሳዳም ሁሴን 142 ሴዎችን አስገደለ ብለው ከነግብረአበሮቹ በስቅላት ያስቀጡት አሜሪካና እንግሊዝ በራሱ በወያኔ ህሳብ 193 ሴዎችን ያስገደለውን መለስ ዜናዊን የቅርብ ወዳጃቸው አድረገው ዋይት ሐውስና ዳውንንግ ስትሬት ፓላስ ስጋብዙት ፤ አንዴ እሱን በሌላ ጊዜ ደግሞ ባለቤቱን ሲሽልሙ ተስተውሏል። ሙጋቤ የተቃዋሚ መሪዎችን አንድ ቀን አስረውና ደብድበው ለቃቃቸው ብለው በከፍተኛ

ዲፕሎማቶቻቸውና ውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤታቸው አማካይነት ቀንና ሌሊት ሲጮኹ የሚሰሙት አሜሪካኖችና እንግሊዞች ከ50 ሺህ በላይ ህዝብ በእስር ቤት ያሳጎረውንና በመቶ የሚቆጠሩ ዜጎችን በጥይት ያስደበደውን መለስ ከ“ድንቅ” የአፍርካ መሪዎች ተርታ መድበው ሲያቅማጥሉት ይሰማል። ታዲያ ወደነዚህ (ቡሽ ፤ ብሌይር ወይም ነገ ለሚተኳቸው…) የሚናሰማው ጩኼት ምን ፋይዳ አለው? የትግላችን ስልት መቀየር አለበት።

እስረኞች የሚፈቱትና የኢትዮጵያ ህዝብ ነፃ የሚሆነው ወያኔን በሁሌገብ ትግል ማለትም በሰላማዊ ህዝባዊ ዐመፅና በወታደራዊ ሄይል ሲናሰገድደው ብቻ ነው። በአሜሪካና በእንግሊዝ ማንኛውም ፓርቲ በሥልጣን ላይ ቢወጣ ድጋፋቸውን የሚሰጡን ወይም የሚነፍጉን በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የሃይል ሚዛን በመመልከት እንደሆነ መረዳት አለብን።

የሃይል ሚዛን ልለውጥ የሚያስችል ስልት ማውጣት የሚችሉት በፖለቲካው ዓለም ያሉት ድርጅቶችና የሙያ ማህበራት (civic societies) ናቸው። ይህም ጊዜ ወስደውበት ተወያይተው የሚያወጡት መሆን አለበት እንጂ በሩጫ ግንባር ፤ ትብብር ፤ ብሔራዊ ርቅና አንድነት ወይም የዚህ ጥሪ የዚያ ጥሪ እያልን ስሙን በወረቀት የሚናሰፈረው ሳይሆን በተገባር ልተረጎም የሚችል በጠንካራ መሰረት ላይ የተጣለ መሆን አለበት ብዬ አምናለሁ። በእሽቅድድም ያለምንም ቅድሜ ዝገጅት በየጊዜው በአንድነት ትግል ስም የሚወጡት መግለጫዎች ፤ ጥሪዎች ፤ ወዘተ በወያኔ መሳቂያ እያደረጉን ነው። ለምሳሌ ፤ በመጋቢት ወር ውስጥ የወጣው “የብሔራዊ እርቅና አንድነት ጥሪ” ያሰባሰበው ፊርማ 1000 እንኳን አልሞላም። እንዲህ ዓይነት ያለተጠና እርምጃ ይጠቅመናል ብዬ አላምንም። ሁሉም ተቃዋሚዎች በአንድ ወጥ በሆነ ግምባር ተጣምረው በጋራ ጠላት ላይ ማነጣጠር አለባቸው። ትግላችን በዋናው ጠላት ላይ ያነጣጠረና ሁሌገብ መሆን አለበት። ለስኬቱ ይረዳሉ ብዬ የገመትኳቸውን የሚከተሉትን ነጥቦች እጠቁማለሁ።

1. በአሜሪካ ፤ በእንግሊዝና በአውስትራሊያ ብሔራዊ ምርጫ በዚህ ዓመትና በሚቀጥለው ዓመት ስለሚካሄድ የገዥ ፓርቲም ሆኔ የተቃዋሚ ፓርቲ ሰነተሮችን ከወዲሁ መያዝና ማሳመን ያስፈልጋል። እኛም በዴሞክራሲያዊ ምብታችን መጠቀም አለብን። ድምፃችንን የምንሰጠው ዓላማችንን ለሚደግፋት መሆኑን ማሳወቅ አለብን፤

2. ወያኔ ህዝብ ያልመረጠው ግን በጠመንጃ አፈሙዝ በሥልጣን ላይ የወጣ ቡድን መሆኑን በቃን ሰለቸን ሳንል በተገኘ መድረክ ሁሉ መናገርና ማጋለጥ፤

3. የተቀናጀና ህለገብ ትግል ማካሄድና ለተገባራዊነቱ በጋራ መንቀሳቀስ፤

4. የእስረኞችን ፊታልን ጥያቄ ማንሳቱ ካልቀረ ሁሉንም እስረኞች ማካታት አለብን። በበኩሌ ወያኔ እስረኞችን በበጎ ፍቃዱ ይፈታል የሚል እምነት የለኝም። እስረኖችን ማስፈታት የሚቻለው ትግሉን በማፋፋምና ለድል በመብቃት ብቻ መሆኑን ተገነዝበው ሁሉም ድርጅቶች ባንድነት መታገል፤

5. የህብረት ትግሉን ባለመሳተፊም ሆነ ባለማገልገል እያደናቀፉ የሚገኙትን ነጥሎ በማውጣት መቃወምና ድጋፍ መንሳት የሁላችንም ሃላፊነት መሆኑን መገንዘብ አለብን፤

6. በተቃዋሚ ፖርቲዎች ውስጥ ወያኔ ሠርገው እንዳይገባ መጠንቀቅና በር መዝጋት ፣ የገቡትም ካሉ ማጋለጥና ማውጣት።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሸንፋል!